# የደሴ ሕዝብ – ተረኛዉ የመስዋዕትነት ጠቦት?

ከመሳፍንት ዘፈረንሳይ ለጋሲዮን (አዲስ አበባ)

(t.mesafint@gmail.com)

ሐምሌ 2001 ዓ.ም

ከሳምንታት በፊት ያደመጥኩት አንድ ዜና በርካታ ነገሮችን ወደ አእምሮዬ እያመላለሰና ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማያዉቅ ስሜት በዉስጤ እየፈጠረ ፋታ ሲነሳኝ ይህችን ወረቀት ጫጭሬ የተሰማኝን ለወገኖቼ ባካፍልስ ብዬ አሰብኩና ብዕሬን አነሳሁ። ዜናዉን አብረን አድምጠነዋል፤ የኔኑ መሰል ስሜት በዉስጣችሁ የፈጠረባችሁ በቁጥር ቀላል እንደማትሆኑ ግምቴ ነዉ። ፈልጌዉ ሳይሆን ፈልጎኝ የመጣዉ ወሬ የቤተሰቤን ታሪክ፣ የግል የህይወት ልምዴን፣ ሁሌም የምናፍቀዉን የወላጆቼን የትዉልድ ስፍራ፣ የክርስትያንና የሙስሊም ዘመዶቼን አብሮ የመኖር ዘይቤ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የአብሮ አደጌን የሰይድን ወንድምነት እያስታወሰኝ በጊዜም በቦታም ሩቅ ይዞኝ ነጎደ።

ተወልጄ ያደኩት አሁን በምኖርባት በአዲስ አበባ ከተማ ቢሆንም ወላጆቼ ስለፈለቁባት ስለወሎ ሰዉ ፊት ይገፎ የምቀርበዉ እዉቀት አላጣም። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ወሎ የሄድኩት እድሜዬ 16 ዓመት ሲደርስ ቢሆንም፤ በየጊዜዉ ከወደዛዉ ብቅ እያሉ ከሚጎበኙን ዘመዶቻችን ጋር አብሮ እየመጣ ሲያዉደኝ ከኖረዉ የአካባቢዉ ሕዝብ ፍቅር እንዲሁም አብሮ የመኖር መዓዛ እየተማረኩ አድጌአለሁ። ወላጆቼ ክርስትያኖች ናቸዉ፤ ነገር ግን ሀረጋቸዉ ወደ ኋላ ቢቆጠር ብዙም ራቅ ሳይባል ሙስሊሞች ይገኙባቸዋል። ጿሚና ጸሎተኛ የነበሩት ክርስትያኑ አያቴ አባቴን የወለዱት ሙስሊም ወላጆች ከነበሯት ባለቤታቸዉ ነዉ። አባቴ የክርስትና እምነት ተከታይ ሆኖ ቢያድግም፤ ይህ ከሙስሊም ዘመዶቹ ጋር አብሮ ለመኖር እንቅፋት ሆኖበት አያዉቅም። ቤተክርስትያን ሳሚዋ እናቴ ሙስሊም ዘመድ አዝማዶቿ ሊጎበኟት ከወሎ ወደ መሀል ሀገር ሲመጡ ጠብ እርግፍ እያለች የሀይማኖታቸዉን ስርዓት በማክበር የክርስትያን ምግብ ባልነካዉ እቃ ምግባቸዉን አዘጋጅታ፣ ለፀሎት የሚሰግዱበትን ስጋጃ አነጣጥፋ እንዲሁም ዱአ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸዉን ሁሉ አቀራርባ ስትቀበላቸዉ እያየሁ አድጌአለሁ። የእናቴ የቅርብ ዘመድ የሆነዉ ሰይድ ትምህርቱን እኛ ጋር ተቀምጦ ሲከታተል የእስልምናም ሆነ የክርስትና በዓላት በመጡ ቁጥር ለእርሱም ለኛም እንደየእምነታችን የሚታረደዉ ታርዶ በዓላቱን በጋራ እየበላን እየጠጣን በማክበር ለዓመታት አብረን ኖረናል።

ወደ ወላጆቼ የትዉልድ ስፍራ ለመሄድ እድል ባገኘሁ ጊዜ ወላጆቼ እቤታችን ያየሁትን አብሮ የመኖር ባህል ምንጭ ወሎ ዉስጥ አገኘሁት። ወደ ወሎ በተለይም ደግሞ ወደ ደሴ በየምክንያቱ ሳቀና እዛ ያሉትን ሙስሊሞቹን ዘመዶቼን ለአፍታ እንኳን ቢሆን ሳላያቸዉ አልመለስም። የሰይድ እናት እንዲሁም እህትና ወንድሞቼ "መሳፍንቴዋ" እያሉ በፍቅራቸዉ እየጠሩኝ፣ አንገቴ ላይ ተጠምጥመዉ በስስት ዓይናቸዉ እያዩኝ፣ እያነቡ ተቀብለዉና አስተናግደዉ እያነቡ ሲሸኙኝ፤ "ምነዉ እዚህ የምቆይበት ጊዜ እንደዓመት በረዘመልኝ" ብዬ ከመመኘት በቀር ሀይማኖታችን ለየቅል መሆኑን ለአፍታ እንኳን አስቤዉ አላዉቅም – እነሱም እንደኔዉ።

ይህ የማወጋችሁ የቤተሰቤ ታሪክ ባጭሩ የወሎ ሕዝብ ታሪክ ነዉ። ሀገራችንን ገላጭ የሆነዉ የሀይማኖቶች መከባበርና መቻቻል ጎልቶ ከሚታይባቸዉ ቦታዎች መካከል ወሎ ግንባር ቀደሙ ነዉ። ወሎ ዉስጥ ሙስሊሙን ከክርስትያኑ፣ ክርስትያኑንም ከሙስሊሙ በስምም ሆነ በግብር ለመለየት አስቸጋሪ ነዉ። ይህን የመሰለ አስደናቂ ትስስር ያለዉ የደሴዉ ወገኔ በመሬት ጉዳይ በተቀባባ ሽር ለወያኔ መርዛማ ሴራ መታጨቱን ያረዳኝን ዜና ስሰማ ነዉ እንግዲህ ያ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት በዉስጤ የተፈጠረዉ። ግና ብዙም ሳልቆይ በአንደኛዉ ጆሮዬ የገባዉን ይህን ወሬ በዉስጤ ተመቻችቶ ሳይቀመጥ ባጫወትኳችሁ ታሪኬ በመምራት ምንገድ ምንገዱን እያሳየሁት "እኔ ግድም ድርሽ እንዳትል" ብዬ በሌላኛዉ ጆሮዬ አስወጣሁት።

ኢትዮጵያችን በአብዛኛዉ የምትታወቀዉ በየጊዜያቱ በሚፈራረቁባት ሰዉ-ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮች ቢሆንም ጥቂት የማይባሉና የብዙዎችን ቀልብ የሚስቡ በጎ ገፅታዎችንም ታድላለች። ከነዚህ መካከል በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችለዉ በሕዝቦቿ መካከል የሚታየዉ የመቻቻልና አብሮ የመኖር ባህል ነዉ። ሀገራችንን ለ19 ዓመታት እንደመዥገር የተጣበቀባት የወያኔ መንግስት ከምንም ነገር በላይ በሚሳሳለት ስልጣኑ ላይ ለመቆየት፤ በመልካም ገፅታዎቹ ኮርቶና ደምቆ የሚኖረዉን ሕዝብ በዘር፣ በጎሳ፣ በሀይማኖት፣ በፆታ፣ በእድሜና በሌሎችም ሰበባ ሰበቦች ለመለያየት ያልሰራዉ ድራማ የለም። ለ19 ዓመታት እንዳየነዉ ወያኔ እንደ እርጉዝ ቀን እየቆጠረ ለመለያያ ካዘጋጃቸዉ ካርዶቹ መሃል አንዱን መዘዝ አድርጎ በሕዝብ ዉስጥ እንደ እባብ በደረቱ ተስቦ እየገባ የፖለቲካ ቁማሩን ሲቆምር ቆይቷል። በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ሕዝብን በደምና በአጥንት አለያይቶ ለማጫረስ እንደሚሞክረዉ ሁሉ፤ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሙስሊሙና በክርስትያኑ መሀል ለዘመናት ሰፍኖ የቆየዉን ሰላምና አንድነት በመናድ ሕዝቡን በታትኖ ስልጣንን ከራሱ ጋር

እንደጠጉርና ማበጠሪያ አስተሳስሮ ለመኖር የልዩነት መርዙዉን እየረጨ ጠብ ለመጫር ይዶልታል – በሚፈጥራቸዉ ግርግሮችም ንፁሀንን ይጨፈጭፋል።

ወያኔ በሀይማኖት ሰበብ የማበጣበጥ ስራ እንዲሰሩለት የሚያደራጃቸዉን ቡድኖች በማር የለወሰዉን ሬት አስይዞ በሕዝብ መሃል እየለቀቀ በተለያዮ መንገዶች ብጥብጥን ይጭራል። አንዱን መስሎ የሌላዉን እምነትና ተከታዮቹን በማንቋሸሽና በመዝለፍ፣ በአምልኮ ስፍራዎችና ሕዝብ በብዛት በሚገኝባቸዉ ቦታዎች የእምነት መፈክሮችን በማሰማት፣ ለአንዱ የሚገባዉን መሬትም ሆነ ሌሎች ነገሮች ለሌላኛዉ በመስጠትና ሌሎች መሰል ሴራዎችን በመሸረብ የሀይማኖቶቹን ተከታዮች ቁጣና ንዴት ዉስጥ እየከተተ ወደ አለመግባባትና ጠብ በመምራት ሕዝብን በሕዝብ ላይ ለማነሳሳት ያሴራል። በእምነቶቹ ተከታዮች መካከል የማግለል አስተሳሰብና አመለካከት የሚያሰርፁ ሀይሎች እንዲሰርጉ በማድረግ ተቻችሎ የኖረውን ሕዝብ ሆድ እያሻከረ ሊያባላዉ ይሸርባል። እነዚህንና መሰል ተግባራትን በማቀነባበር በሕዝብ መሀል እሳቱን ከለኮሰ በኋላ ቅልብና አልሞ-ተኳሽ ሰራዊቱን ሴራዉን ወደሸረበበት ስፍራ እየላከ ንፁሀንን አስቀጥቅጦና አስገድሎ ሲያበቃ የአዞ እንባዉን በማንባት "ድርጊቱን የፈፀሙት የፖለቲካ ሴራ ያላቸዉ የጥፋት ሀይሎች ናቸዉ" እያለ እንደ ጲላጦስ እጁን በአደባባይ ይታጠባል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ይህንኑ መርዙን ለመርጨት ከሞከረባቸዉና ሙስሊሞችና ክርስትያኖች ተቻችለዉ ከሚኖሩባቸው ቦታዎች መካከል ለአብነት ሀረርን፣ ጅማን እንዲሁም አዲስ አበባን መጥቀስ ይቻላል።

ነገር ሳላበዛ ከላይ የጠቀስኩትን ርካሽ የወያኔ አካሄድ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ አንድ የማስታዉሰዉን ታሪክ አጫዉቻችሁ ልለፍ። ጊዜው የ97 ምርጫ መዘዝ ናላውን ያዞረው ወያኔ የቅንጅት መሪዎችን በግፍ እስር ቤት ያጎረበትና ያንንም ተከትሎ ህዝቡ በድብቅም በግልጽም ተቃውሞውን እያሰማ በነበረበት ወቅት ነዉ:: በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካባቢ ከፍተኛ የጭንቀት ድባብ የረበበት ጊዜ:: ወያኔ በዚህ ወቅት የሕዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየርና ራሱ የነዛውን የዘር መርዝ ተቋቁሞ አንድ ሆኖ የተነሳውን ህዝብ ለመከፋፈል እንደለመደው ለክፉ ቀን የሚጠቀምባትን የሀይማኖት ካርድ መዘዝ አድርጎ ቁማሩን ለመጫወት ሞክሮ ነበር:: የሴራው አቀናባሪዎች በጅማ ዩኒቨርስቲ "አንድ ተማሪ ቅዱስ ቁርዓንን ቀዶ ለመጸዳጃነት ተጠቀመ" የሚል የበሬ ወለደ ወሬ በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች መካከል እንዲናፈስ ያደርጋሉ:: አጀንዳው የተፈለገው ወዲህ ነበርና ወሬውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥም በትጋት አሰራጭተውት በቀጣዩ ቀን ሙስሊም ተማሪዎች ይህንን በማውገዝ ሰልፍ እንዲወጡ ያደርጋል:: በዚህም ምክንያት ጉዳዩን ከምንጩ ያልተረዱ ሙስሊም ተማሪዎች ክፉኛ ተቆጡ፣ የትምህርት ሂደቱም ተስተጓጎለ:: በወቅቱ በመገረም

እጄን በአፌ ላይ አድርጌ የተመለከትኩት ሌላ ክስተትም ነበር - እኔ በነበረኩበት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አንድ ዲፓርትመንት ውስጥ ትሰራ የነበረች ወያኔ የአስተዳደር ሰራተኛ ከተማሪዎቹ ጋር ሰልፍ ውስጥ ተቀላቅላ በአይኔ በብረቱ ተመለከትኳት::

ወያኔ ዛሬም ለተመሳሳይ ተልዕኮዉ ሴራዉን ሸርቦ በተረኛ የመስዋዕት ጠቦትነት ወደመረጠዉ ወደደሴ ሕዝብ ተሽሎክሉኮ ለመግባት ሞክሯል። በደሴ ሙስሊሙን ከክርስትያኑ ለማጋጨት የተመረጠዉ አጀንዳ መሬት ነዉ። ቀድሞዉንም መንግስትና ሕዝብ እያወቀዉ በድንኳን ቤተክርስቲያን ከልለዉ ፈጣሪያቸዉን ሲያመልኩበት በነበረዉና አሬራ ሰፈር አዘዋ ገደል ጫፍ በሚገኘዉ ስፍራ ላይ የቤተክርስቲያን ሕንፃ ለመገንባት በአግባቡ ጥያቄ ላቀረቡት የክርስትና እምነት ተከታዮች ወያኔ በሎሌዎቹ በኩል “ሙስሊሞች ስለተቃወሙ ቦታዉ ለቤተክርስቲያን ግንባታ ሊዉል አይችልም” በማለት ሙስሊሞቹ ያላሉትን አሉ ብሎ ዓይን ባወጣ መልኩ ሕዝቡን ለማቃቃርና ወደጠብ ለመግፋት በመሞከር እንደለመደዉ የቻለዉን ያህል ንፁህን በጥይት ጨረሰ። ሴራዉን ጠንቅቆ የተረዳዉ ሕዝብ የተላከበትን የወያኔ ቅልብ “ወግድልኝ! ሳልደርስብህ አትንካኝ” ከማለት ዉጪ ሙስሊሙን ወንድሙን “መሬቴን ለምን አስከለከልከኝ?” ብሎ እሰጥ አገባ ዉስጥ አልገባም። የወሎ ክርስትያንና ሙስሊም ሕዝብ እንኳንስ መሬት ይገባኛል ብሎ ወያኔ የሚመኝለትን ዓይነት ጠብ ዉስጥ ሊገባ ይቅርና፣ በአንድ ቤተ-አምልኮ ዉስጥ ፈጣሪዉን በጋራ ማመስገን የማይሳነዉ በደምና በፍቅር የተሳሰረ ሕዝብ ነዉ።  ይህ ሕዝብ እንኳንስ ለጠብ ደርሶ በዚህ በዱርዬ መንግስት ገላጋይነት ሊዳኝ ይቅርና፣ ተቻችሎ መኖር ላልገቸባዉ ለነዚህ ደናቁርት የአብሮ መኖርን ፊደል የሚያስቆጥር ሳይማር ያወቀ ሕዝብ ነዉ። በጥምቀት በዓላት የወሎ ሙስሊም “አልሀምዲሊላህ ታቦታችን ገባ” ይላል ተብሎ የሚነገረዉ በቁምነገር መነፅር ሲታይ የሚኖረዉን መልዕክት የሚገልፀዉ ይህንኑ ነዉ። በወሎ ፀንቶ የኖረዉ የክርስትያኖችና የሙስሊሞች አንድነት ተምሳሌትነቱ ስለሀይማኖት መቻቻል ብቻ ሳይሆን ስለሀይማኖት መዋሀድም ጭምር ነዉ። በደምና በአጥንት አንድ የሆነዉን ሕዝብ በሀይማኖት ልለየዉ ብሎ መቃዠት ስንጥቅ የሌለዉን ብርጭቆ ሰባራ ነዉ ብሎ እንደማለት ይሆናል።

ወገኖቼ፣ ይህ መንግስት በሕዝብና በሀገር ላይ እየፈፀመ ያለዉ የግፍ መዓት “ሀረግን ሲመዙት ሀረግ ይከተለዋል” አይነት ሆኗል። ሀገራችን ኢትዩጵያ የምትታወቅባቸዉና ዜጎቿ የምንኮራባቸዉ በጎ ገፅታዎቿ አንድ በአንድ እንደጉም በነው እንዲጠፉ እየተደረገ ነዉ። እንደ ብሔር ብሔረሰቦቿ ሁሉ በሀይማኖቶቿ ብዛትና በአማኞች ተቻችሎ የመኖር ባህል ደምቃ የምትታየዉ ኢትዩጵያችን፣ ይህ ገፅታዋ በሀይማኖት ግጭቶች ለሚታመሱ ሀገራት ትምህርት ሰጪ ሊያደርጋት ሲገባ ወያኔ ጠብመንጃ ሲፈታበት በኖረ እጁ ጥላሸት ሊቀባዉ

ደፋ ቀና ይላል። በሀይማኖት ሰበብ የሚነሳ ቅራኔ እጅግ አውዳሚና በቀላሉ ድንበር ተሻጋሪ እንደመሆኑ ሀይማኖትን እያራገቡ የፖለቲካ ቁማር ለመጫወት መሞከር ዉጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ለእናንተ ለማስረዳት አይዳዳኝም። ዛዲያ እንዲህ አይነቱን የወያኔ ሴራ "ሳይቃጠል በቅጠል" የማለት ሀላፊነት የማን ይሆን?

የልዩነት አባዜ የተጠናወተዉና፤ እየሰነጣጠቀ ለማፍረስ፣ አያላላ ለማዉለቅ የማይተኛዉ ይሄ ወንበዴ መንግስት ትናንት በዘር፣ ዛሬ ደግሞ በሀይማኖት ሊለየን ጉድጓድ እንደሚምሰዉ ሁሉ፤ ነገ ከእንቅልፉ ሲባንን "ባልና ሚስቶች በጾታ ስለሚለያዩ አብረዉ መኖር አይችሉም" ብሎ ቢል በበኩሌ አልገረምም። ቁም ነገሩ አንድ ነገር በተፈጠረ ቁጥር "ይህን ከሚያሰማኝ ምነዉ ሞቼ በነበር" ማለቱን አቁመን፤ ሽሚዛችንን ሰብሰብ፣ መታጠቂያችንን ጠበቅ አድርገን ለመፍትሄ መንቀሳቀስ ሰብዓዊና ሀገራዊ ግዴታችን መሆኑን መረዳቱ ላይ ነዉ። "ዘጠኝ ሞት ቢመጣ አንዱን ግባ በለዉ" በሚል አኳኋን የሀገራችንን ጉዳይ ዳር ይዞ ለመታዘብ መምረጥ በተለይ በዚህ ቀዉጢ ሰዐት ከማንም ዜጋ የሚጠበቅ አይሆንም። ለራሳችን ነፃነት ብሎም ለሀገርና ለወገን ሰላምና አንድነት ሊከፈል የሚገባዉን መስዋዕትነት ከፍለን ይህን የተመረዘና የተበላሸ ስርዓት የማስወገድ የቤት ስራ አለብን ጎበዝ!። ወያኔ የሕዝብን አንገት ሊቀላበት ቀጥቅጦ የሚስለዉ ካራ እራሱ አንገት ላይ የሚያርፍበትን ጊዜ የማቅረብ ሀላፊነት የማንም ሳይሆን የኛዉ የራሳችን ነዉ።

ፈጣሪ ሀገራችንን ይጠብቅ፤ እኛንም የአላማና የዉጤት ሰዉ ይበለን!